ሰኔ ፲ ቀን 2009 ዓ.ም.

የአማራ ህዝብ መድህንን ንቅናቄ(አህመን) ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ

የአማራ ህዝብ መድህንን ንቅናቄ(አህመን) ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሰኔ ፲ ቀን 2009 ዓ.ም
ባደረገው ልዩና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በአቶ ሰፊው አማራ ከሚመራው ቤተ አማራና ውጭ አገር ካለው አዴሃን ጋር ሊደረግ የነበረውን ውህደት የደረሰበትን ደረጃና የተጋረጠውን ችግር መርምሮ አህመን እንደ ድርጅት ሊከተለው የሚገባውን የወደፊት አቅጣጫ ወስኗል፡፡

ድርጅታችን አህመን ከአምስት ወር በፊት የአማራው ህዝብ ትግል የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ካለን የጋለ ምኞት የተነሳ ከቤተ-አማራ እና በውጭ አገር ካለው አዴህን ጋራ በመዋሀድ ቤተ አማራ መድህን በሚል ስያሜ ውህድ ድርጅት በመፍጠር የአማራን ህዝብ ከተጫነበት የአፓርታይድ አገዛዝ ነጻ ወጥቶ በቀደመ ልእልናው እንዲኖር ለመታገል አዲስ የጋራ አመራር ግልጽ በሆነ ፕሮግራም ላይ ታዛቢወች በተገኙበት እንደመሰረትን ይፋ መደረጉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ይሁን እንጅ የውህዱ ድርጅት አመራር ከመመረጡና የተወሰኑ መግለጫዎች በውህዱ ድርጅት ስም ከመውጣታቸው በቀር ውህደቱ በተግባር ሊረጋገጥ አልቻለም።

ለዚህም ዋናዋና ማሳያዎች ቀጥለው የተጠቀሱት ናቸው።

1. ፕሮግራሙ በውህደታችን ማግስት ለአባላት እንዳይሰራጭ መታገዱ፤
2. የአህመን ሙሉ መዋቅር እስካሁን ድረስ ለብሔራዊ ምክር ቤትና ለስራ አስፈጻሚነት ከተወከሉት በቀር ውህደቱ ከተፈረመ በርካታ ወራት ቢቆጠሩም በውህዱ ድርጅት አለመታቀፉ፤
3. ሙሉ ለሙሉ ከአህመን እምነትና ከውህደት ስምምነታችን ያፈነገጡ መጣጥፎች ቤተ አማራን ወክለው የምክር ቤት አባላት በሆኑ አመራሮች በተደጋጋሚ ዛሬም ድረስ እየተለቀቁ መሆናቸው
4. የውህዱ ድርጅት አመራር ሙሉ በሙሉ የአገር ቤቱን እንቅስቃሴ የረሳና ከአንድ እጅ ጣት ቁጥር በታች በሆኑ ጥቂት የዲያስፖራ እንቅስቃሴወች ብቻ መገደቡ፡
5. የአማራውን ህልውና ልእልና በኢትዮጵያ ጥላ ስር የማስከበርና የአማራን ኢትዮጵያዊነት የማይደራደር ግልጽ አቋም ተይዞ እያለ  በስብሰባዎቻችን መካከል የኢትዮጵያን ስም በቃል ደረጃ ማንሳት እንኳ የሚያሸማቅቅበት ደረጃ ላይ መደረሱ፤
6. ተስማምተን የተዋሃድንበት ፕሮግራም በህገ ወጥ መንገድ ተከልሶ የጋራ መታገያ ራዕያችን የአማራን ሕዝብ ህልውናና መብት አንድነቷና ዳር ድንበሯ በተከበረ ኢትዮጵያ ውስጥ ማስከበር የሚለው ተስማምተን የተዋሃድንበት ራዕይ ሙሉ በሙሉ የድርጅቱን ደንብ በጣሰ ሁኔታ ከራዕዩ እንዲወጣ መደረጉ፤
7. በአህመን አመራር ተጀምረው ወደመሬት ወርደው እንቅስቃሴ የተጀመረባቸው ድላችንን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያፋጥኑና የትግላችንን የመጀመሪያ ምእራፍ ለመቋጨት የሚያስችሉ ኦፕሬሽኖች ተቋርጠው መቅረታቸው።
8. በደንባችን ውስጥ በህዝብ ግንኙነት መምሪያ ስር መዋቀር ያለባቸውን የድርጅቱን ዌብሳይትና የፌስቡክ ገጽ ፓስወርዶች ሊቀመንበሩ በህገ ወጥ መንገድ ከህዝብ ግንኙነት ሀላፊው ነጥቆ ወገንተኛ በሆነ መንገድ ራሱ ሊቀመንበሩ ከመጣበት ድርጅት ከቤተ አማራ ለመጣው ለውጭ ግኙነት ሀላፊው መስጠቱ፤
9. መሬት ላይ የወረዱ ሥራዎችን እንድንሰራ በተደጋጋሚ ብንወተውትም ሰሚ በመታጣቱ፡ ወዘተ።
10. የስብሰባ ስርዓትና የደንብ ጥሰት በተከታታይነት እየተፈጸመ ስራ ሲስተጓጉልና ስብሰባ ሲታወክ ለማስተካከል በሞከሩ አህመንን ወክለው ወደ ስራ አስፈጻሚው በተላኩ አባሎቻችን ላይ በተደጋጋሚ ጊዜ ስድብና ዘለፋ እየተፈጸመባቸው መሆኑና ይህም እስካሁን ድረስ የቀጠለ መሆኑ፤
11. ከምንም በላይ የውህደቱን ስምምነት ከፈረሙ ድርጅቶች ከአንደኛው ከመጡ ወኪሎች በተደጋጋሚ የተስተዋለው የአቋም መዋዠቅና የታማኝነት ጥያቄን የሚያስነሱ ምልክቶች ደጋግመው ከመታየታቸውም በላይ በቅርቡ ደግሞ የወያኔ

አሸከር ሁኖ የአማራን ህዝብ እያስፈጀ ያለውን ብዓዴንን አትንኩብን ማለትና ለብዓዴን መሪዎች በግልጽና በአደባባይ ጥብቅና ቆመው መታየታቸው ዱሮውንም የአላማ አንድነት ነበረን ብለን ያመንነው በስህተት እንደነበረ ከማረጋገጣችንም በላይ ከሰው በላው ስርዓት ጋር በሙሉ ቁርጠኝነትና ወኔ የምንታገል ወገንና ሀገር ወዳድ የአማራ ልጆች ህቡነታችን የመጋለጥና በቀላሉ የመመታት አደጋ እንደተጋረጠበት ለማስተዋል ችለናል፡፡

ሌላወ ቀርቶ በርካታ አባሎቻችን ሲታሰሩና ሲሰወሩብን እንኳን ይህንን ሊከታተል የሚችልና አቋም የሚወስድ አመራር ማግኘት አልቻልንም። በዚህም ምክንያት ጥቂት የምክርቤት አባላት በውህዱ ድርጅት ውስጥ የነበራቸውን ውክልና በራሳቸው ፍላጎት  አንስተው ከህላፊነታቸው ለቀዋል።

ከዛሬ ነገ መፍትሄ ይገኛል ብሎ በትግስት ሲጠባበቅ የነበረው አመራርና አባልም ስሜቱ ከመከፋት ወደ ቁጣ እየተቀየረ በመምጣቱ በስራ አስፈጻሚነት ለወከልናቸው አመራሮች በተደጋጋሚ የውህደቱ እንቅፋት የሆኑ ችግሮች ጥርት ባለ ሁኔታ ተፈትተው ወደ ቀደመ ተግባራዊ ትግል አቅማችንን አጠናክረን እንድንመለስ ካልሆነም ፈጣን አቋም ወስደን ተግባራዊ ካልሆነው ውህደት ወጥተን ትግላችንን በቀደመው ወኔና መንፈስ እንድንቀጥል ብንጠይቅም፤ "ትንሽ ታገሱን ሁሉም በአጭር ጊዜ መስመር ይይዛል" ከሚል ማዘናጊያ ያለፈ መፍትሄ ማግኘት አልቻልንም።

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የአህመን የአገር ቤት የቀጠናወችና የዞን አመራሮች ውጭ አገር ካሉ የዞን አመራሮች ጋር በመቀናጀት ደንቡን ተከትለን ልዩና አስቸኳይ የመላው አባላት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ አድርገን የሚከተሉትን ውሳኔወች አስተላልፈናል።

ሀ) ***<u>ውህደቱን በተመለከተ</u>***

1) ውህደቱ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊሆን ባለመቻሉ፥
2) አህመን የማይደራደርባቸው መሰረታዊ የሆኑት አማራነትን ከኢትዮጵያዊነት ጋር ማለትም የአማራን ሕዝብ ህልውናና ብሄራዊ ጥቅሞችና መብቶች በኢትዮጵያ አንድነት ውስጥ ማረጋገጥ የሚለውን እምነታችንን ማንጸባረቅ የሚወገዝበት አስተሳሰብ አካል መሆን ስለማንችል፥
3) መተማመን ባልሰፈነበት አሰራር ውስጥ መቀጠሉ የአገር ቤቱን መዋቅር ሙሉ በሙሉ አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ፥
4) ትግላችን ከውህደቱ ማግስት ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ የተገደበ በመሆኑ፥

ድርጅታችን ተጀምሮ ሊጠናቀቅ ካልቻለው የውህደት ሂደት ራሱን እንዲያገልልና አህመን ተጠናክሮ ትግሉን እንዲቀጥል ወስነናል።

ለ) በቤተ አማራ መድኅን ውስጥ አህመንን በሥራ አስፈጻሚነትና በምክር ቤት አባልነት እንዲወክሉ የተመደቡ አባሎቻችን የተሰጣቸውን ኃላፊነት አንስተናል።

ከአህመን ጋር ተመሳሳይ የፖለቲካ አቋም ካላቸው የአማራ ድርጅቶች  ማለትም አማራነትን ከኢትዮጵያዊነት ጋር አጣምሮ መሄድን ወይም የአማራን ሕዝብ ህልውናና ብሄራዊ ጥቅሞችና መብቶች በኢትዮጵያ አንድነት ውስጥ ማረጋገጥ አቋማቸው ከሆነ እና ወያኔን ለማስወገድ ጽኑ አቋም ካላቸውና የተግባር እንቅስቃሴ ካላቸው ድርጅቶች ጋር ግን አብረን በአንድነት እና በትብብር እየሰራን ትግሉን መቀጠል አለብን በማለት ወስነናል፡፡

የአማራ ሕዝብ መድሕን/ አሕመን ጠቅላላ ጉባኤ